የጤና ሚኒስቴር

# የ2019 ኣዲስ የኮሮና ቫይረስ በሽታ (COVID-19)

በዲሰምበር 31፡ 2019 ዉሃን በምትባለው፡ የቻይና ከተማ፡ ያልተመረመረ የሳምባ-ምች ሁኔታዎች እንደታዩ፡ የጤና ጥበቃ ባለ ስልጣኖች ኣሳወቁ። የዚህ የሳምባ-ምች፡ መነሻ ደግሞ፡ ኣንድ ከዚህ በፊት በሰዎች ታይቶ የማይታወቅ፡ የ2019 ኣዲስ የኮሮና ቫይረስ በሽታ በመባል የሚታወቀው እንደሆነም፡ ተረጋገጠ።

## ይኽ የ2019 ኣዲስ ኮሮና ቫይረስ በሽታ ምንድን ነው፧

ኮሮና ቫይረስ ተብሎ የሚጠራው፡ ኣንድ ዋና የቫይረስ ቤተስብ ሆኖ፡ ከተለመደው የጉንፋን በሽታ ጀምሮ፡ እስከ የባሱትን የመንተፋሻ ኣካላት ተላላፊ በሽታዎች፡ እንደ ብሮካይቲስ፣ የሳምባ-ምችና (ኑሞኒያ)፡ ከባድና ኣጣዳፊ የመተንፋሻ ኣካላት በሽታ (ሳርስ) የመሳሰሉት በሽታዎች፡ ምንጭ የሆነ ቫይረስ ነው።

የ2019 ኮሮና ቫይረስ በሽታ (COVID-19) የተላላፊ የሆኑትን የመተንፈሻ ኣካላት በሽታ ጠንቅ ሆኖ፡ በሁበይ ኣውራጃ (ዉሃን) የጀመረ ነው።

በኦንቴርዮ፡ የመጀመርያው ግምታዊ የኮሮና ቫይረስ በሽታ፡ በ ጃኑዋሪ 25: 2020 ነው የተገኘው።

ስለዚህ የ2019 ኣዲስ ኮሮና ቫይረስ በሽታ፡ በጥልቀት ለማወቅ ከፈለጋችሁ፡ በበይነ-መረብ ኣድራሻችን፡ ontario.ca/coronavirus በመሄድ ማየት ትችላላችሁ።

## የኮሮና ቫይረስ በሽታ ምልክቶች፡ ምን ምን ናቸው፧

የዚህ የ2019 ኣዲስ ኮሮና ቫይረስ በሽታ ምልክቶች፡ ከተለመዱት የጉንፋን በሽታ ምልክቶች፡ እስከ ከባድ የሆኑ የመተንፈሻ ኣካላት በሽታ የሆኑትን፡ ያካትታል። እነሱም፥

- ትኩሳት
- ሳል
- የመተንፈስ ችግር።

ይኽ የ2019 ኣዲስ ኮሮና ቫይረስ በሽታ የሚስከትላቸው ችግሮች፡ እንደነ የሳምባ-ምች (ኑሞኒያ)፤ የኩላሊት መድከም/መሞትና፡ እስከ ሞት ድረስ ነው።

የምታዩባችሁ የብሽታ ምልክቶች፡ ከተለመዱ የጉንፋን በሽታ ምልክቶች የባሱ ከሆኑና (ለምሳሌ፡ ትኩሳት፣ ሳልና የእስትንፋስ እጥረት)፡ ምልክቶቹ ሲጀምሩ ደግሞ፡ በሁለት ሳምንታት ውስጥ፡ በብሽታው ተበክለው ባሉት ኣከባቢዎች፡ ተጉዛችሁ ከነበረ፡ በኦንቴርዮ የጤና መስመር 1-866-790-0000 በመደወል፡ ወይም ደግሞ የኣካባቢያችሁ ሕዝባዊ የጤና ኣገልግሎት ማዕከል (Public Health) በ (health.gov.on.ca/en/common/system/services/phu/locations.aspx በመሄድ ተገናኙን። የሚሰማችሁና ምልክቶቹ በሙሉ ደግሞ ንገሩዋቸው።

የ2019 ኮሮና ቫይረስ በሽታ ከተበከሉት ኣካባቢዎች[1]፡ የተመለሳችሁ ከሆነ፡ ለኣስራ ኣራት ቀናት በቤት ተዘግታች ሁ መቆየት ኣለባችሁ። ምናልባት ለበሽታው የተጋለጣችሁ ከሆነ፡ በቤት መዘጋትና፡ ከሌሎች ሰዎች የምታደርጉት ግንኙነቶች መቀነስ፡ በሽታው ወደ ሌሎች እንዳይተላለፍ ለመግታት ይረዳል። እባካችሁ፡ ባካባቢያችሁ ከሚገኘው፡ ሕዝባዊ የጤና ኣገልግሎት ማዕከል በ (health.gov.on.ca/en/common/system/services/phu/locations.aspx በመሄድ፡ ኣስፈላጊ ምክር ይጠይቁ።

የድንገተኛ የፈጣኝ እርዳታ የሚያስፈልጋችሁ ከሆነ ግን፡ 911 በመደወል፡ የሚታዩባችሁ ምልክቶችና፡ የተጓዛቹባቸው ኣከባቢዎች ጠቁሟቸው።

## ይኽ ቫይረስ፡ እንዴት ይተላለፋል፧

ዋና የኮሮና ቫይረስ በሽታ,የሚተላልፍበት መንገድ፡ ከሰዎች ከሚደረጉ የቅርብ ግኑኝነቶች ነው። ለምሳሌ፥ በቤታችሁ፣ በመስሪያ ቦታዎቻችሁና: በጤና ኣገልግሎት ማዕከሎች።

## ከዚህ የ2019 ኣዲስ ኮሮና ቫይረስ በሽታ: እራሴን እንዴት መጠበቅ እችላለሁ፧

ኣሁን በዚህ ጊዜ፡ ለዚህ የ2019 ኣዲስ ኮሮና ቫይረስ በሽታ የሚሆን: የክትባት መድኃኒት የለም።

በየቀኑና በየሰዓቱ ማድረግ የሚገቡንና፡ በሽታው እንዳይተላለፍ ለመግታት የሚረዱን፡ የመከላከልያ ዜዴዎች ግን ኣሉ።

- እጆቻችን በቀን ብዙ ጊዜ በሳሙናና በውኃ መታጠብ፡ ወይም ደግሞ፡ ኣልኮሆል ባለበት የንጽሕና ፈሳሽ ኣድርገን፡ እጆቻችን ማጽዳት
- ስናስነጥስ ወይም ስንስል፡ ለኣፋችን በእጆቻችን እጅጌዎች ማፈን
- ዓይኖቻችን፣ ኣፍንጫችንና ኣፋችን ከመነካካት መቆጠብ
- በዚህ በሽታ ከተጠቁት ሰዎች፡ ኣለመገናኘት
- ኣንተ እራስህ በቫይረሱ የተጠቃህ ከሆነ ደግሞ፡ ከቤት ኣለመውጣት።

---

[1] ስለ በዚሁ ኣዲስ የኮሮና ቫይረስ የተበከሉት ኣገሮች ለማወቅ ከፈለጋችሁ፡ በ Ontario.ca/coronavirus በመሄድ ያንብቡ።

በቫይረሱ በተበከሉት ኣካባቢዎች ጉዞ ለማድረግ ዕቅድ ካለችሁ፡ ወደሚከተሉት ቦታዎች ከመሄድ ይቆጠቡ፥

- ለኣደጋ በጣም ከተጋለጡ ቦታዎች፡ እንደ እርሻ  ቦታዎች፣ የከብቶችና ሌሎች እንስሶች ገበያ፣ እንስሶች ከሚታረዱበት ቦታዎችና፡ ስጋ ቤቶች።
- ከሞቱት ይሁን በሕየውት ካሉ እንስሶች፡ እንደ ኣሳማ፣ ደሮችና ወፎች ሁሉ ኣለመገናኘት።
- የእንስሶች ደምና ሰገራ ከነካቸው ገጽታዎች መጠበቅ።

## ለዚህ የ2019 ኣዲስ ኮሮና ቫይረስ በሽታ የሚሆን መድኃኒት ማግኘት እችላለሁ ወይ፧

ለዚህ በሽታ የሚሆን የተለየ መድኃኒት ወይም ክትባት የለም። በዚ በሽታ የተጠቁት ኣብዛኞቹ ሰዎች፡ ከዚህ ከተለመደ የኮሮና ቫይረስ በሽታ፡ በራሳቸው ቀስ ብለው ይድናሉ።

ለመከላከል ይኸል፡ ማድረግ ያሉብን ነገሮች ግን ኣሉ፥

- ብዙ ውኃ መጠጣት
- ብዙ ዕረፍትና እንቅልፍ ማግኘት
- የቆሰለ ጉሮሮኣችን ለማዳን ደግሞ፡ ገላችን በሙቅ ውኃ መታጠብና:  በቤታችን የእርጥበት ኣብናኝ መጠቀም።

### በጉዞ መኃል እያለሁ፡ ወይም ደግሞ ከጉዞየ ከተመለስኩ በኃላ፡ ከታመምኩስ፡ ምን ላድርግ፧

በጉዞ መኃል እያለህ፡ ወይ ከተመለስክ በኃላ ከታመምክ፡ መጀመርያ ከስዎች ከመገናኘት መቆጠብ ይኖርብሃል። በኦንቴርዮ የጤና መስመር ቁጥር 1-866-797-0000   በመደወል፣ ወይም ባካባቢህ ከሚገኘው፡ ሕዝባዊ የጤና ኣገልግሎት ማዕከል  በመሄድ፡

- የበሽታህ ስሜቶችና ምልክቶች
- የት ኣከባቢ ተጉዘህ እንደነበር
- ከእንስሶች ደግሞ የቅርብ ግኑኝነት ከነበሩህና (ለምሳሌ፡ የከብቶችና ሌሎች እንስሶች የሚሸጡበት ገበያ ሄደህ ከሆነ)፡ ወይም ደግሞ በበሽታም ከተበከለ ሰው ማንኛውንም ዓይነት ግንኙነት ከነበረህ፡ መንገር ኣለብህ።

ወደ ካናዳ ስትመለስ፡ በኣውሮፕላን እያለህ፡ ወይም ደግሞ ኣዎሮፕላኑ ካረፈ በኃላ ከታመምክ፡ ለበረራ ኣስተናጋጆች፡ ወይም ደግሞ፡ ለየካናዳ የድንበር ኣገግሎቶች መኮንኖች፡ መንገር ይኖርብሃል።

ስለ ጉዞህና ስለ የ2019 ኣዲስ ኮሮና ቫይረስ በሽታ በተመለከት፡ ጥልቅ እውቀት እንዲኖርህ ከፈልግክ፡ በ travel.gc.ca/travels/advisories/pneumonia-china  በመሄድ፡ ማምበብ ትችላለህ።

## በኣዲሱ ቫይረስ ተጤቅቻለሁ ብዬ ካሰብኩስ፡ ምን ላድርግ፧

የኣዲሱ የ2019 ኣዲስ ኮሮና ቫይረስ በሽታ ስሜቶቻና ምልክቶች ከታዩብህ፡ የጤና መስመር 1-866-790-0000 በመደወል፡ ወይም ደግሞ የኣካባቢያችሁ ሕዝባዊ የጤና ኣገልግሎት ድርጅት (Public Health) በ (health.gov.on.ca/en/common/system/services/phu/locations.aspx ተገናኙ። የሚሰማችሁና ምልክቶቹ በሙሉ ደግሞ ንገሩዋቸው።

የድንገተኛ የፈጣኝ እርዳታ የሚያስፈልጋችሁ ከሆነ ግን፡ 911 በመደወል፡ የሚታዩባችሁ ምልክቶችና፡ የተጓዛቹቧቸው ኣከባቢዎች ጠቁሟቸው።